# ተባይን እናጥፋ!

***በአጭሩ:***

- ተባዮችንለማሰስ ጊዜ ይስጡ፡፡
- ተባዮችን ሲያስሱ የሚከተሉት ዕቃዎ ይዘዋል:
    - መብራት
    - የካርድ መጫወቻ ወይም ክረዲት ካርድ
    - ክብ ማስትሽ
    - ጨርቅና ለብ ያለ ውሃ
    - የፕላስቲክ ቦርሳዎች
    - የፍራሽ ማስቀመጫ
- ከተባይ ያጸዱት ዕቃ የሚያስቀምጡበት ንጹህ ቦታ ያዘጋጁ፡፡
- ተባዮችን ያስሱ
    - በሚቀመጡበትና የሚተኙበት ቦታ
    - በፍራሽ፣ ቦክስ ስፐሪንግ፣ አልጋ ፍሬምና የአልጋ ልብሶች ላይ
    - በአልጋ ዕቃዎች በሚገኙ ቀዳዳዎችና ክፍት ቦታዎች፣ ቤዝ ቦርዶች፣ መስኮቶች፣ የበር ፍሬሞችና የኤሌክትሪክ ማስተላለፍያዎች ተባዮችን ያስሱ
- ተባዮችን ሲያስሱ የሚያገኟቸው ተባዮች መያዝ ወይም መግደል አለብዎት
- ይህ ዘዴ ሁሉም ተባዮችን አይገድልም ነገር በቤትዎ ውስጠው ያሉ ተባዮች ቁጥር እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

ያስታውሱ ተባዮቹ በጣም ትንሽ፣ ለጥ ያለ ቅርጽ ያላቸውና ፈጣኖች ናቸው:

**ለበለጠ መረጃ ዘ ቤድ ቤግ የመረጃ መስመር (Bed Bug *InformationLine* )በ 612-624-2200 ይደውሉ ፣ bedbugs@umn.edu ይጠቀሙ ወይም www.bedbugs.umn.edu ይጎብኙ፡፡**

# ተባይን በእጅ መቆጣጠር

ራስዎን ያድርጉት፣ ተበይን የመቆጣጠር ስራ የሚጀምረው ተባዮቹን በከታተልና በማስወገድ ወይም በመቆጣጠር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ስኬታማ እንዲሆኑ በትዕግስት ተባዮቹን ሊደበቅባቸው የሚችሉ ቦታዎችን ይመልከቱ፡፡ ይህ ዘዴ ሁሉም ተባዮች በአንድ ጎዜ አይገድላቸውም፡፡በዚህ ስልት በተደጋጋሚ ካደረጉት ተባዮቹን ሁሉም ተባዮች መግደል ባይችሉም የተባዮቹን ቁጥር መቀነስ ይችላሉ፡፡

**ተባዮቹን ለመግደል የሚያስፈልግ መሳርያዎች**
ተባዮቹን በቀላሉ ለመግደል የሚያስፈልጉ መሳርያዎች በመደብሮችና በመኖርያ ቤትዎ አከባቢ ይገኛሉ:

- **መብራት:** ተባዮች በጨላማ ቦታዎች እና ቀዳዳዎች እንዲሁም ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይደበቃሉ፡፡ አብዛኛው ጊዜ ተባዮች የጨለማ ቀይማ ወርቃማ ዓይነት ቀለም አላቸው፣ ነገር ግን ምግብ ካልተመገቡ ቀላል ወርቃማ ቀለም ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ይህ ለማየት አስቸጋሪ ያደርጋቸዋል፡፡ ተባዮቹን ለመቆጣጠር ከተጠቃው አከባቢ ትዩዩ መብራት ከተጠቀሙ እንቁላልና ትናንስ ተባዮች በቀላሉ ለማግኘት ያደርጋል፡፡
- **ያገለገለ ወይም አሮጌ ክሬዲት ካርድ:** ይህ የፕላስቲክ ወይም የፕላስቲክ ነክ ካርድ ጫፉ ከቀዳዳዎችና ክፍት ቦታዎች ገፍቶ ለማስወጣት ያስችላል፡፡ የካርዱ ጫፍ በቀዳዳዎችና ክፍት ቦታዎች በማንቀሳቀስ ተባዮቹን በመግፋት መያዝ ወይም መግደል ይቻላል፡፡
- **ክብ ማስትሽ**: ሰፋ ያለ፣ ንጹህ ስለሆነ የፕላስቲክ ሽፒንግ ጥሩ አማራጭ ነው፣ ምክንያም ተባዮቹን ለያዝ ስለሚያስችላነ አቅርቦ በማሳየት ተባዮች መሆናቸው ለመለየት ስለሚያግዝ ነው፡፡ ተባዮቹን ከተመለከቱ ወይም በቀዳዳዎችና ክፍት ቦታዎች ሲቆፍሩ ተባዮቹን ለማውጣ ስለት ነገር ይጠቀሙ፡፡



- **ልብስና ሙቅ ውሃ:** ልክ እንደ ማስቲሽ ሙቅ ውሃ ያለው ውሃ ተባዮቹን ለመቆጣጠር ሊያግዝ ይችላል፡፡ በመያዣ ውሃ በመያዝ ቦታውን በማጽዳት ልብሱ የሚገኝበት ምድር ቤት ተባዮቹን እንዳይኖሩበት ያረጋግጡ፡፡ እያጸዱት ባለው ምድር ቤት ውሃ ከባዛብዎት ከመጠን በላይ የሆነውን ውሃ በጨርቅ ያጽዱት፡፡ በተጨማሪ ያጸዱትን ቦታ መልሰው ይመልከቱት፣ ምክንያቱ ምናልባት ሙቀቱ የተራቡ ተባዮች ሊንቀሳቀሱ ሊያደርግ ስለሚችል፡፡ ይህ ልብስ በተለይ ተባዮች በተሰባሰቡበት አከባቢ ውጤታማ ነው፡፡ እርጥበት ያለው ምድር ቤት የ ውጤታማነት እንደሚቀንሰው ያስተውሉ፡፡
- **ፕላስቲክ ቦርሳዎች:** የገበያ ቦርሳዎችና የቆሻሻ ቦርሳዎች ምናልባት በተባይ የተጠቁ ልብሶች ለመያዝ ጠቃሚ ነው፡፡ የተጠቁ ዕቃዎች በቦርሳ ውስጥ መክተት ዕቃዎቹ ሳይሰፋፉ ወደ ሌላ ቦታ እንዲሰፋፉ ለማስቀመጥ ያግዛል፡፡
- **የፍራሽ ማስቀመጫዎች:** የፍራሽ ማስቀመጫዎች ትላልቅ "የጨርቅ ቦርሳዎች" ሆነው ፍራሹን በውስጣቸው ለማስቀመጥ የሚያግዙ ናቸው፡፡ መቆለፍያቸው ከተዘጋ በኋላ ተባዮቹ የሚበሉትን አጥተው ይራባሉ፡፡ በቤትዎ ለእያንዳንዱ ፍራሽና ቦክስ ስፐሪንግ ማስቀመጫውን ሊኖርዎት ይገባል፡፡ በማስቀመጫው ውስጥ ወይም ቦክስ ስፐሪንግ ተባዮች ካሉ በሁለት ሳምንታት ውስጥ መሞት ይጀምራሉ ፣ ይሁን እንጂ ማስቀመጫው ለ18 ወራት መጠቀም ይገባል፡፡



የተለያዩ ዓይነታት ማስቀመጫ ያሉ ሲሆን ተባዩን ለመቆጣጠር የሚያስችል ማስቀመጫ መጠቀምዎን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡

# ተባይን እናጥፋ!

**ንጹህ ዞን መመስረት**

የተባዮችን ፍለጋ ለመጀመር የተጠቁ እቃዎችና ንጹህ እቃዎች የሚቀመጡበት ቦታ በመለየት የመጠቃት ዕድል መቀነስ ይገባል፡፡

የክፍት ግንብ ኮርነሮችና ጫፎችና ላይ ይጀምሩ፡፡ ካርድ ተጠቅመው ከቀዳዳዎችና ክፍት ቦታዎች መቆፈር ከቻሉ ይሞክሩት፡፡ በቀዳዳዎችና ክፍት ቦታዎች ላይ ይስሩ፡፡ ለምሳሌ በምድር ቤት ያለውን ቤዝ ቦርድ እየዳሰሱ ከሆነ በቤዝ ቦርዱና በምድር ቤቱ መካከል እንዲሁም በቤዝቦርዱ ራስና ግንብ ካርድ ማግኘት ከቻሉ ይመልከቱ፡፡ የባር ታይል( bare tile) ወይም የእንጨት ምድር ምድር ቤት ካልዎት ወለሉን ለማጽዳት እርጥብ ጨርቅን መጠቀም ይችላሉ፡፡ ከመጠን በላይ ውሃ አይቀሙ፡፡ ወለሉን ካጸዱ በኃላ ያለውን ማንኛውም የሚንቀሳቀስ ነገር ይመልከቱ፡፡ ምንጣፍ ያላቸው ቦታዎች ካሉ የጸዱ ቦታዎች ክፈት ያድረግዋቸው፡፡ *" ተባዮችን ለመቆጣጠር ክፍት የሚተው ነገሮች" የሚል በ* (www.bedbugs.umn.edu/bed-bug-control-in-residences/vacuuming-to-capture-bed-bugs) *ይመልከቱ፡፡ በዚህ ግድግዳ ላይ የሚገኙ ስዕሎችና ሌሎች ነገሮች መመልከትዎን አይዘንጉ፡፡*

አሁን እርስዎ ሌሎችዕቃዎች ለመዳሰስና ወደ ንጹህ ቦታ ለማስቀመጥ ተዘጋጅተዋል፡፡ ዕቃዎች ወደ ንጹህ ቦታ ማድረግዎ ሲቀጥሉ አብዛኛው ክፍል ክፍት ይሁንና ንጹህ ዞኑን ይሰፋፋል፡፡ ይህ ዘዴ ዕቃዎችና ቁሳቁሶች ከሁለት ጊዜ በላይ አያነሱም ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ዕቃ ከማጓጓዝ ይልቅ በተባይ ፍለጋ ላይ እንዲያነጣጥሩ ያግዝዎታል፡፡



የተባይ ምልክት ይኖር እንደሆነ የፍራሹን ጫፍና መአዝኖችን ይመልከቱ፡፡

መታጠብ ያለባቸው ልብሶች፣ የአልጋ ልብሶችና ሌሎች ቁሳቁሶችን በአንድ ላይ ይሰብስቡ፡፡ ትንሽ ነገሮችን መዳሰስ ማለት የቀለለ ስራ ነው፡፡ *" ተባዮችን የሚገድሉ ቁሳቁሶች" የሚል ይመልከቱ* (www.bedbugs.umn.edu/bed-bug-control-in-residences/laundering-bedbug-control)

**መፈለግ**

የተባዮችን ፍለጋ በራስዎ ዕቃዎች ላይ ይጀምሩ፡፡ ምን እየፈለጉ እንደሆነ ያስታውሱ: ትላልቅ፣ ትናንሽ ተባዮች፣ እንቁላል፣ የደረቁ ቆዳዎችና ምልክቶች ያላቸው ቦታዎች፡፡ ተባዮቹ እንዴት እንደሚለዩ የበለጠ መረጃ ለማግኘት*"ተባይ አግኝቻለሁ?"*(www.bedbugs.umn.edu/have-i-found-a-bed-bug) የሚለውን ይመልከቱ፡፡

ትራሶች፣ ቦክስ- ስፐሪንግ እና የአልጋ ፍሬምን ጨምሮ ከአልጋዎ ላይ ይጀምሩ፡፡ መጀመርያ የሚታዩ ነገሮችን ይዳስሱ፡፡ ሁሉም ጫፎችና ኮርነሮች ይመልከቱ፡ ሁሉም ጫፎችና የአልጋ ይዘታዎችን ይመልከቱ፡፡ ፍራሹ በአልጋው ላይ እያለ በአምስት ጎኖቹ ሊታይ ይችላል፡፡ የላይኛው ክፍል ማየት ከተጠናቀቀ በኃላ ፍራሹን በማቆም የታችኛው ክፍል ማየት ይችላሉ፡፡



ቦክስ ስፐሪንግ ሲያጸዱ ቲኪንጉን ያጥፉት

ይህ የቦክስ-ስፐሪንግም በተመሳሳይ መልኩ ይድገሙት፡፡ ልዩነቱ ቦክስ ስፐሪንግ በታችኛው ክፍል የታጠበቀ " ቲኪንግ(ticking)" የሚባል ጨርቅ የተሸፈነ የፕላስቲክ ጫፍ ያው መሆኑ ነው፡፡ የቦክስ ስፐሪንግ ታችኛው ክፍል እነዚህ መገጣጠሚያዎችና ጫፍ ተመሳሳይ የተባይ የመደበቂያ ቦታዎች ናቸው፡፡ በቦክስ ስፐሪንጉ ውስጥ ምንም ተባይ እንደሌላ ለማረጋገጥ በእንጨቱ ውስጥ ያለውን ቲኪንጉን ማስወገድና ቀዳዳዎች፣ ክፍት ቦታዎችና በቦታው ያሉ ጉድጓ መሰል ነገሮች ማስወገድ አለብዎት፡፡ ከዳሰሱት በኃላ ቲኪኒንጉ በቦታው ሊገጠም ይችላል፡፡

የብረት ፍሬም እንኳ ቢሆን ሁሉም ጎኖች ይመልከትዋቸው፡፡ ፍሬሙን የሚገናኝበትና ማንኛውም የተደረበ ቦታ ላይ ትኩረት ያድርጉ፡፡  የራስጌና የግርጌ ቢታዎች ተባዮች የሚገኙባቸው ዋና ዋና ቦታዎች ናቸው፡፡ ሁሉም ወሎች በጥንቃቄ ይመልከቱ፣ በሁሉም ዕቃዎች ላይ የሚገኙ ቀዳዳዎች፣ ክፍት ቦታዎችና መሰል ነጎረች ይመልከትዋቸው፡፡


በአልጋው ጠርዝና የተባይ ምልክቶች ካሉ ይመልከቱ

አልጋውን ከጨረሱ በኃላ በክፍሉ በሚገኘው ሌላ ዕቃ ላይ ይቀጥሉ፡፡ መጀመርያ ትልቅ ዕቃን መመልከትና ማጽዳት ተመራጭነማ ምክንያቱም በወለሉ በንጹህ  ቦታ ቦታ ላይ ደህንነቱ ተጠብቆ ለማስቀመጥ ሌሎች ዕቃዎች በትላልቅ ዕቃዎች አጠገብ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ቅድሚያ በሚታይ ቦታ ላይ ባሉ ዕቃዎች ይጀምሩ፡፡ ሁሉም መዓዝኖችና ተደራቢዎችን ይመልከቱ፡፡ ሁሉም ክፍሎችና ክፍት ቦታዎች በጥንቃቄ ይመልከቱ፡፡ ዕቃው ከግንቡ ያንቀሳቅሱትና ጀርባውን ይመልከቱት፡፡ ከደጋፊ ቦርድ የሚያገናኝ ተደራራቢና ማንኛውም ቀዳዳዎችን ይመልከቱ፡፡

ማንኛውም ተሳቢ በማስወገድ ሁሉም መዓዝኖችና ጫፎች ይመልከቱ፡፡ ሁሉም ዕቃዎች ከታሳቢ በማስወገድ ወደ ላውንደሪ ወይም ሌላ ተገቢ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ይሰብስቧቸው፡፡

ዕቃው ባዶ ሲሆን የታችኛው ክፍል ማየት ይኖርብዎታል፡፡  ዕቃውን ለማንቀሳቀስና በጎኑ ለማስመጥ ሊያግዝዎት ይችላል፡፡ ዕቃውን ለመንከባከብ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጋቸውን ያስተውሉ- በወለሉና በዕቃው መካከል ለስለስ ያለ ደጋፊ ዕቃ መጠቀም ይገባል፡፡

ሁሉም ቦታ እስከሚጸዳ ድረስ ሁሉም ዕቃዎችና ቁሳቁሶች ማጽዳትዎን ይቀጥሉ፡፡ ሁሉም ነገር ለማዘጋጀት ንጹ ቦታ ሁለት ወይ ሶስት ጊዜ ማስፋት ሊያስፈልግዎት ይቻላል፡፡  ንጹህ ቦታ ለማስፋት የመጀመርያው ንጹህ ቦታ ለመፍጠር ያደረጉትን ተመሳሳይ ደረጃዎች

በክፍሉ ላይ የሚገኙ ሁሉም ዕቃዎች አጽድተው ካጠናቀቁ በኃላ በክፍሉ  በንጹህ ቦታ የማይገኙ ሌሎች ዕቃዎችን ያጽዱ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ቤዝ ቦርዶችና ማንኛውም ክፍት ቦታና ቀዳዳ ያጽዱ፡፡

ካጠናቀቁ በኃላ ዕቃዎችዎን መልሰው አስገብተው የማጽዳት ስራዎን ያከናውኑ፡፡  ማንኛውም ያልታየ ነገር በመቆጣጠርያ መንገዶች ማለፍ አለበት(ማቀዝቀዝ፣ማሞቅ) ወይም ዕቃው ለመንቀል ማስብ አለብዎት፡፡

የፍራሽ ማሸቀመጫው በፍራሹና በቦክሽ-ሽሪነጉ እንዲያስቀምጡ ይመከራሉ፡፡ የፍራሽ ማስቀመጫዎች  ደግመው የሚያጸዱት ቦታ ይቀንሳል ፣ እንዲሁም በቀጣይ ተባዮችን በቀላሉ ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡

መስከረም 29 ቀን ተሻሻለ  2014

በAmelia Shindelar እና Dr. Stephen Kells, 2011
ፈንድ ለ"ተባይን እናጥፋ" ዘመቻ በአሜሪካ የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲና MDA ፈንድ የተደረገ ነው፡፡ ከሚኒሶታ የጤና ክፍል የተገኘው ተጨማሪ ድጋፍም የሚደነቅ ነው፡፡በአሜሪካ አካል ጉዳተኞች ውል መሰረትይህ መረጃ  በ651/201-6000 በመደወል ከጠየቁ በአማራጭ የኮሚዩኒኬሽን አገባብ ማግኘት ይችላሉ፡፡ የ TTY ተጠቃሚዎች የሚኒሶታ የግንኙነት አገልግሎት በ711 ወይ 1-800-627-3529 መደወል ይችላሉ፡፡

የሚኒሶታ ዩኒቨርሲቲና MDA በማስተማሪነትና ሰራተኝነት እኩል ዕድል አላቸው፡፡